# ለኢሳት ስርጭት አዘጋጆች ቅን ማሳሰቢያ
# ከይልማ በጋሻዉ

፩ኛ/ *መንደርደሪያ*

ታላቁ ጥላሁን ገሠሠ ባንደኛዉ እንጉርጉሮዉ ‵ሦስት አልማዞች አሉ′ ብሎ ነበር። አንደኛዋም፤ ሁለተኛዋም ሦስተኛዋም አልማዝ አንድ ሆነዉ ስላስቸገሩት ነበር (እነዚያም የደርግ ፋሺስታዊ መንግስት መስራቾች እነመንግሥቱ፤ አጥናፉን ሲሳይ ለማለት ነበር)። ሦስቱም አልማዞች አንድ ሴይጣን አምባገነኖችና ነፍሰገዳዮች ስለነበሩ አገራችንንም ጭምር ለወያኔ ሸጠዉ ያለቁትም አለቁ የተረፉትም ፈርጥጠዉ ወጥተዉ ይኖራሉ። አፋቸዉን ዘግተዉ ተደብቀዉ መኖር ሲገባቸዉ አሁንም መጽሐፍ ተብዬ መጣጥፎችን እያስጻፉ ያላግጡብናን፤ ይቸበችቡብናል። ያ መልእክት ዛሬ ደግሞ ትንሽ ፊቱን አዙሮ ሁለት አልማዞች ሆኖ የቀረበ ይመስለኛል፤ እነሱም ኢሳትና ግንበት ይመስሉኛል። በሁለቱ መካከል ስላለዉ አንድነት የማያቅ ሀቀኛ ዜጋ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ነገር ግን በሆነ ምክንያት አንድነት ሳይሆን ሁለትነትን ከመረጡና ከጠቀማቸዉ መብታቸዉ ነዉ። ነገር ግን ሃቁን ተናግረዉ አንድነታቸዉን መስክረዉ ከሌሎችም ታጋዮች ጋር ቢተባበሩ አገራችንን ቶሎ ለማዳን በተቻለን ነበር ብዬ አምናለሁ። እስካሁን ድረስ ዉድ አገራችንን  ነፃ ለማዉጣት ያልቻልነዉ ህብረት በመላላቱ ምክንያት ብቻ ነዉ። አሁንም እየተበጣጠስን አለን አለን እያልን የዉጪ መንግሥታትና ወያኔ ስልጣን ላይ እንዲያወጡን ብንጠብቅ ትልቅ  ኃጢአት ይመስለኛል። በዘገየን ቁጥር የህዝባችን ሰቆቃ እየባሰበት ነዉ የሚሄደዉ። አገራችን እነደአገር የማትኖርበት ሁናቴ ሊፈጠር ይችላል። መሬቶቻችን ለባእዳን በርካሽ ዋጋ እየተቸበቸቡ፤ ድንበሮቻችን  ሲደፈሩና የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ተጋይተዉ  ምድረበዳ ሆነን ተቀረን በኃላ ሥልጣን ተብዬ የሴይጣን በረከት ቢጎናጸፉ ዋጋ የለዉም፤ መምቢን ካስታወሳችሁ (መንበሬ በየነ) እንዲህ ብላ አንጎራጉራ ነበር፤ ‵አንጀቴ ተቆርጦ ከሆዴ ከወጣ፤ እንግዲህስ ሃኪሙ ምን ሊቀጥል መጣ?′

፪ኛ/ ባብዛኛዉ የምታቀርቧቸዉ ሰዎች የደርግና የወያኔ ካድሬዎችና ተገንጣዮች ለምን ይሆናሉ?

በየቃለ ምልልሶቻችሁ ባብዛኛዉ የምናያቸዉ ግለሰቦችና ቡድኖች በህዝባችን ላይ ከፍተኛ ወንጀል ሠርተዉ  የተላኩ የደርግና የወያኔ ካድሪዎች ናቸዉ። የመንግሥቱ ቀኝ እጆችና ወገን ሻጮች (ፈላሾችን ጭምር)፤ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስር ሳሉ ስንት ግፍ የሠሩ ካድሬዎች (የባእሉ ግርማ ሕይወት ጭምር)፤ የወያኔን ጄነራሎች አስተማርኩ፤ የህዝብ ድምፅ አጭበረበርኩ የሚሉ የወያኔ ካድሬዎች (ሚንስቴ ደ ኤታዎች) ጭምር በእጃቸዉ ገና ያለደረቀ የህዝባችን ደም አለባቸዉ። አምድ አገኙ፤ ሰዎች መሰሉ፤ ጭራሹንም እኛዉ ካላስተማርናችሁ ማለት ጀመሩ። ጨርሶ ልክ አይደለም። እግዚአብሔር አይወደዉም። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ንስሐ እስከሚገቡ ድረስ ተደብቀዉ ቢቆዩ መልካም ነበር። እኔ በበኩሌ ፊታቸዉን ባየሁና ድምፃቸዉን በሰማሁ ቁጥር እጅግ ያመኛል። መጥኔ ይስጣቸዉ። ንቀት አያብዙብን አደራ።

በተፈራረቁት አረመኔ መንግሥታት እጅ ስንቶቹ ቢረግፉም እኮ ጥቂት በሕይወት የተረፉ ንፁሓን ዜጎች አሉ። ላገር ጥቅም ከሆነ ምነዉሳ ነፍሰ ገዳዮችንና ካድሬዎቻቸዉን ብቻ ሳያሆን እነዚህንም ንፁሓን አገር ወዳዶች አቅርባችሁ የማታናግሯቸዉ? የሚከተሉትን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ብታቀርቡላቸዉ ለወጣቱ ትዉልድ ትክክለኛዉን ታሪክና መልካም እርአያነት አስረክበዉ ባለፉ ነበር፤

- የተማሪዉ እንቅስቃሴ እንዴት ነበር?
- መሬት ላራሹ ለምን ተባለ?
- የዚያ ዘመን እጅግ የነቃዉ ወጣት የከፈለዉ መስዋእትነት ለምን ነበር?
- የህዝቡስ ትግል ለምን ተነጠቀ?
- ህብረት ለምን ላላ?
- ወደፊትስ ህዝባችንን ለማዳን ባንድነት ምን ማድረግ አለብን?
- ወዘተ

በፋሺስት የደርግና የወያኔ አስተዳደሮች ዉስጥ አልተሳተፉም እንጂ ሃቁ እነርሱ ዘንድ እንዳለ መዘንጋት አይቻልም።

፫ኛ/ *መደምደሚያ*

- የደርግም ሦስት አልማዞች አላዋጡንም
- ያሁኖቹም ሁለት አልማዞች በወያኔና በዉጪ መንግሥታት አካባቢ ቆመዉ ረዥም የህዝባችንን ሰቆቃ ዘመን ከሚመለከቱ ወደህብረት ተመልሰዉ የሃቁ ትግል አካላት እንዲሆኑ እማፀናለሁ።
- ቀድሞዉንም እየዘለሉ ገብተዉ የወያኔን ቻርተር የፈረሙ፤ ወያኔን ለሥልጣን ያበቁና ጥቂትምም ብትሆን ጊዜያዊ ሥልጣን የተካፈሉ ሆድ አደሮች ነበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች፤ አሁንም ልቦና ይስጣቸዉ። ተዉን እንላቸዋለን።

- ህዝባዊ ትግል እያኮላሹ ወደሥልጣን መጠጋት፤ መዉጣት፤ እንደገና ተለማምጠዉ ለመጠጋት መሞከር እጅግ ከፍተኛ ኃጢአት እንደሆነ ህዝባችን ለይቶ አዉቆ የዲሞክራሲና የነፃነት ትግሉን ማፋፋም አለበት ራሱ ነዉ፤
- ቸሩ አምላችን ከፖሊቲካ ነጋዴዎች ይሰዉረን፤ ዉድ አገራችንን ይጠብቅልን፤ አሜን።